መሰናበታቸው ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በአብላጫ ድምፅ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ትርጉም ላይ ያለውን ቅሬታ በመጥቀስ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር "ማንኛውም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል የሚያጠቃልል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት የድንጋጌው ተፈፃሚነት ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው ብሎ መተርጎሙ አግባብ ባለመሆኑ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው ድርጅቶችም ተፈፃሚነት አለው በሚል ተተርጉሞ ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 712(1(ሀ)) ጋር ተገናዝቦ ተመርምሮ በዚህ ችሎት ትርጉም እንዲሰጥበት በዚህ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ለብቻው፤ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በጋራ ሰኔ 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ዘርዘር ያለ ሲሆን አጠቃላይ ጭብጥ በሁለት ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የመጀመሪያው የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች ስር የተቀመጡት መመዘኛዎች የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆናቸው እና የአራጣ ብድር ተሰጥቷል የተባለው ለማህበር በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በአተረጓጎም ረገድ የፈፀመው ስህተት የለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው በስር ፍርድ ቤቶች በነፃ የተለቀቁት ከተበዳይ ጋር ተራ የብድር ውል ግንኙነት እንጂ የአራጣ ብድር ያልነበረ ለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 14/2011 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረበውን የቅሬታ ነጥብ የሚያጠናክርበትን ምክንያት በማከል በቀረበው ቅሬታ መሰረት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪዎች በተከሰሱበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 712 ስር "ማንም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት የሚመለከት እንጂ የተባዳዩን ማንነት የሚገልፅ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ያለበት የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መፀሃፍ፣ ምዕራፍ ሶስት፣ ክፍል ሶስት "የጉሊናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" በሚል አርዕስት ስር በመሆኑ ዞሮ ዞሮ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀምበት ተበዳይ ሰው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በህግ አስተምህር ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር/ድርጅት/ ስለመሆኑ በችሎቱ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በልዩ ዓላማ የመብት እና ግዴታ ባለቤት እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም የሚንቀሳቀሰውም ሆነ ስራውን የሚከውነው በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት ነው፡፡ ድርጅቱን ለማንቀሳቀስ በህግም ይሁን በውል ስልጣን የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ ለድርጅቱ ጥቅም እና መብት እስከሰራ ድረስ በተሰራው ስራ ተጠቃሚውም ሆነ ተጎጂው ድርጅቱ ይሆናል፡፡

ይህ በመሆኑም ነው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በተለያየ የወንጀል ተሳትፎ ደረጃ ወንጀል አድርገው በተገኙ ጊዜ በእንደራሴዎቹ የተሳትፎ ደረጃ ልክ ድርጅቱ እራሱ ወንጀል

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 28-02-1

እንዳደረገ ተቆጥሮ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣ ስለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3) እና 34 ስር የተደነገገው፡፡ እናም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት የመብት እና ግዴታ ባለቤት በመሆኑ በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል ተከስሶ ሊቀጣ እንዲሁም እንደማንኛውም የተፈጥሮ ሰው የወንጀል ድርጊት ተጎጂ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ትርጉም የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በባህሪያቸው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆኑ ድንጋጌው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት ተፈፃሚነት የለውም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳዩን ችግርተኝነት፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን ወይም መንፈሰ ደካማነቱን ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት በአማራጭ መስፈርትነት የተቀመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ በትክክልም የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ አግባብነታቸው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካልም የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለአብነት ያክል "መንፈሰ ደካማነት" እና "የበታችነት" የሚለው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን "ችግርተኝነት ወይም የገንዘብ ችግር" የተባለው ደግሞ ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡

እናም የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮቹ በአማራጭነት የተቀመጡ በመሆናቸው እንደ ነገሩ ሁኔታ እና አግባብነት መመዘኛው ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ተግባራዊ ከሚደረግ በቀር ድንጋጌው ተፈፃሚነቱ ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው የሚባል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በቀረበበት አግባብ ተረጋግጧል አልተረጋገጠም የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሆኖ በድርጊቱ ተበዳይ ተብሎ የተጠቀሰው የንግድ ማህበር እንደራሴዎች በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከተጠሪዎች ሲበደሩ የነበረው ድርጅቱ አጋጥሞት በነበረው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑን ከክርክሩ አጠቃላይ አመጣጥ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአንድ ድርጅት እንደራሴዎች ድርጅቱ ባጋጠመው የገንዘብ ችግር ምክንያት በአራጣ ገንዘብ ከተበደሩ እና ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጥ ከተቻለ የንግድ ድርጅቱ በአራጣ ወንጀል ድርጊት ተበዳይነት የማይጠቀስበት ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የትግራይ ሰበር ችሎት የወንጀል ህጉን አንቀፅ 712 የተረጎመበት መንገድ የድንጋጌውን አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀሉን ድርጊት በተመለከተ ማስረጃና ፍሬ ነገርን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያላቸው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ማስረጃዎች መርምረውና መዝነው በተጠሪዎች እና በተበዳይ ድርጅት መካከል የነበረው ግንኙነት የተራ ብድር እንጂ የአራጣ ብድር አለመሆኑን ያረጋገጡ ለመሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ከማለት ባለፈ የስር ፍርድ ቤቶች የአራጣ ወንጀል አልተፈፀመም ለማለት በተጓዙበት መንገድ እና በደረሱበት ድምዳሜ ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ምን እንደሆነ ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎችን ነፃ በመልቀቅ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ

ፊርማ ቀን 28-02-12

## ውሳኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል ተፈፃሚነት የተፈጥሮ ሰው በሆነ ተበዳይ ላይ ብቻ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሮ የተቀረው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 195(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በወንጀል ህግ አንቀፅ 712 ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡

## ትዕዛዝ

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/መ

የሰ/መ/ቁጥር 159407

የካቲት 27 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳኜ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ተማስ ብርሃኑ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቢኒያም ደበበ አሸግሬ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ። የክሱ ይዘት፡- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 የተመለከተዉን በመተላለፍ ተጠሪ የማይገባዉን ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ መጋቢት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 11:00 ሰዓት ሲሆን በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 05 ቀበሌ 08/09 ክልል ልዩ ቦታዉ ሚካኤል ማደሪያ አካባቢ ወላጅ እናቱ የሆነችዉን የግል ተበዳይ ባዩሽ ጥላሁንን በእጇ ይዛዉ የነበረዉን ቦርሳ ለመቀማት እንዲያመቸዉ የግራ እጇን ጡንቻ በሀይል አጥብቆ ይዞ ሲታገላት ቦርሳዉን መሬት ላይ ስትወረዉረዉ እሷን በሀይል ወደ መሬት ገፍትሮ በመወርወር ቦርሳዉን ከመሬት ላይ አንስቶ በዉስጡ የነበረዉን ብር 1,100 አዉጥቶ በመዉሰድ ሮጦ ያመለጠ በመሆኑ በፈጸመዉ የዉንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ።

ትክክለኛ ግልባጭ

ፊርማ [illegible] ቀን [illegible]

አንዲቀጣ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም። በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል።

ዉሳኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 178138 ታሕሳስ 12 ቀን 2010 ዓ.ም እና ታሕሳስ 20 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 154251 መጋቢት 26 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ጸንቷል።
2. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቁ

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን [illegible]

ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

***************************************************************************************************************
****************************************************************************************************

እያወቀች ሀሰተኛ ቃል በመስጠት እና የቃለመሀላ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ በመስጠት በመሆኑ የወ/ሕ/አ/452/2/ ስር የተገለፀውን የወንጀል ድንጋጌን የሚያቋቁም ነው፡፡

በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ልትከላከል ብሎ መከላከል ባለመቻሏ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናት ሲል የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ የህግ ስህተትም ያልተፈፀመበት በመሆኑ የበላይ ፍ/ቤቶችም የጥፋተኝነት ውሣኔውን እና ቅጣቱን ማጽናታቸው እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በአብላጫ ድምጽ ጥፋተኝነቱን አጽንቶ ቅጣቱን መንደቡ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ የቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. የትግ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 106413 ህዳር 18 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ፍርድ፣ ውሣኔ እና ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 191/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሳ/ፀ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 06/04/12

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ወስኗል።

3. ስልጣን ያለው ሌላ ችሎት አመልካች ባሉበት ክርክሩን እንዲያይ እና ዓቃቤሕጉም ክሱን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት እንዲያቀርብ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 202 መሠረት ተወስኗል።

## ትዕዛዝ

- አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርበው በዋስትና ላይ እስኪከራከሩ ድረስ ለብር 10,000 / አሥር ሺህ/ የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 ሲያስይዙ ከእስር እንዲለቀቁ በአብላጫ ድምጽ ታዟል።

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በሌሉበት ታይቶ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ባሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በዚህ ችሎት እንዲያስይዙ የተወሰነውን የዋስትና ገንዘብ ማስያዛቸው ሲረጋገጥ በሌላ ጉዳይ የማይፈለጉ መሆኑን አረጋግጦ ከእሥር እንዲለቅ ታዟል።

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ

ሳ/ፀ

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 15

የሰ/መ/ቁ 104511

መጋቢት 30 ቀን 2007

**ዳኞች፡-** አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-1. ዳኜ ሀይሉ ⎫ ጠበቃ ታየ ቀረበ

2. በከልቻ መኮንን ⎭

ተጠሪዎች፡-1. አለምሰገድ ሀብታሙ - የቀረበ የለም

2. ታሪኩ ተክሌ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካቾች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካች የዕቁብ ሰብሳቢ 2ኛ ተጠሪ ዳኛ እና ጸሀፊ፤ ተጠሪዎች አባል በመሆን1ኛ ተጠሪን በ01/01/2005 ብር 50000 ደርሶአቸዉ 2ኛ ተጠሪን 08/07/2005 ዓም ብር 60,000 ደርሷቸዉ ከቡሌ ሆራ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክእንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ባንክ ሄደዉ በቂ ገንዘብ የለም በመባላቸዉ አመልካቾች በጋራ እና በተናጥል ይክፈሉንበማለት ጠይቋል፡፡አመልካቾች ባለመቅረባቸዉ በሌሉበት በማየት ተጠሪዎች የእቁቡ አባል መሆናቸዉን በማረጋገጥ በተጠቃሹ ቼክ ባንክ ቤት ሄደዉ ገንዘቡን በማጣታቸዉና አመልካቾችም የዕቁቡ ሀላፊዎች በመሆናቸዉ 110,000.00 ብር ለተጠሪዎች የመክፈል ሀላፊነት አለባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማከራከር የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡በመጨረሻም ጉዳዩን ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ በአዋጅ ቁ. 25/1988 መሰረት የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸዉን ሲገልጹ፡-በስር የቀረበዉ ክስ የነበረዉ ያልተከፈለኝ የእቁብ ገንዘብ እንዲከፈለን፤ የሚል ሆኖ ሳለ ክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 5(7) መሰረት መዝጋቱ ባግባቡ አይደለም፤ አመልካቾች የእቁብ ጸሀፊና ሰብሳቢ ናቸዉ በማለት፤ በምስክር ሳይጣራ ክፊሉ መባላችን ሊታረም ይገባል፤ ቼኩ የተፈረመዉ በስር ተከሳሽ በነበሩት

አቶ ቦጋለ ግዛዉ ስም ነዉ፤አመልካቾች ከቼኩ ጋር ግንኙነት የለንም፤ አልሰበሰብንም፤ የዕቁቡ ዳኛ መሆኑንና የሚመለከተዉ መሆኑን አዉቆ ጠፍቶ እያለ የአሁን አመልካቾችን ሀላፊ ናችሁ መባላችን ስህተት ነዉ፣ የዕቁብ ደንብ ለዕቁብተኞች ዉል ነዉ ፤እኛ ደግሞ ከዉልም ሆነ ከህግ የመነጨ ግዴታ የለብንም፣ ስለዚህ ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾች እና ተጠሪዎች ክርክር በቼክ አማካኝነት የተሰጠን የዕቁብ ገንዘብ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ ሊከፈለን ባለመቻሉ ይከፈለን በማለት የጠየቁት ዳኝነት የክልሉ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁ.25/88 መሰረት ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸዉ መልስ መስጠት መብታቸዉ ታልፎ በአመልካቾች የቀረበዉን ቅሬታ እና የስር ክርክርን አይተናል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰዉን ይመስላል፡፡ በመሆኑም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንግዲህ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የስር ክርክርን እንዳየነዉ ተጠሪዎችባቀረቡት ክስ በአመልካቾች ሰብሳቢነት፤ ጸሀፊነት እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ዳኛ በሆኑበት የእቁብ አባል በመሆን እቁብ ደርሷቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ እንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ቡሌ ሆራ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በመሄድ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ መዉሰድ ባለመቻላቸዉ አመልካቾች በቼክ የተጠቀሰዉን ገንዘብ በአንድነትና ነጠላ እንዲከፍሏቸዉ በጠየቁት መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማከራከር ዳኝነት ቢሰጡም በመጨረሻ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት ክርክሩ ከቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አዋጅ ቁ 25/88 5(7) በመጥቀስ ቅሬታዉን ሰርዞታል፡፡በዚህም ችሎት ሊታይ የሚገባዉ ነጥብ ሆኖ የተገኘዉ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ያለማስተናገዱን አግባብነት ነዉ፤ በመሆኑም የግራቀኙ መሰረታዊ ክርክር ዕቁብን ተከትሎ ያዋጡት ገንዘብ የመክፈያ ቀኑ ደርሶ አመልካቾች የእቁቡ አመራር በመሆናቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት ስላላቸዉ ቼክ ቆርጠዉ በሰጧቸዉ መሰረት ወደ ባንክ ቤት በመሄድ ገንዘባቸዉን ባለማግኘታቸዉ የዕቁቡን ግንኙነታቸዉን መሰረት አድርጎ እንዲመለስላቸዉ የቀረበ ዳኝነት እንጂ የክርክሩ መሰረት ቼክ ነዉ በማለት አይደለም፡፡ ቼክ የዕቁብ ገንዘቡ ላለመከፈሉ ማረጋገጫ ሆኖ በተራ ሰነድ ማስረጃነት የቀረበ እንጂ በዋናነት ቼኩ ራሱ በንግድ ሕጉ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን አተገባበር ለመመርመር የሚያስችል ክርክር በሚያስነሳ መልኩ የቀረበ ያለመሆኑን ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት የእቁብ ገንዘብን ይከፈለኝ ጥያቄ መሰረት አድርጎ ቼኩን በተራ የሰነድ ማስረጃነት የቀረበበት ሁኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራቀኙን የተጠየቀዉን ዳኝነት እና የክርክሩን አቅጣጫ ባላገናዘበ መልኩ ጉዳዩ በአዋጁ ቁ.25/88 ስር የሚታይ ነዉ ሲል የሰበር አቤቱታውን ሳይመለከተው መዝገቡን መዝጋቱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ ክልሉ ከፍተኛ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበላቸዉ የዳኝነት ጥያቄ አከራክረዉ ዉሳኔ ላይ ቢደርሱም የክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄ ከወዲሁ ስልጣኔ አይደለም ,በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የክርክሩን ይዘት ያላገናዘበ

በመሆኑ ትዕዛዙ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በኦሮሚያ ክልል የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 08843 በቀን 18/10/2005 ዓ/ም እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 168299 በቀን 26/9/2006 ዓ/ም የሰጡትን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 34(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ጉዳዩ በክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዩ በመሆኑ የክርክሩ ይዘትም የፌዴራል ጉዳይ ሊባል የማይችል፣የቼክ ጉዳይ ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡

3. የግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

## ውሳኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 106030 ሕዳር 05 ቀን 2011 ዓ/ም፣ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23805 የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ/ም እና የመቐለ ከተማ ሠሜን ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14758 ጥር 04 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

2. ተጠሪዎች ብር 91,666.60 ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ 15% ወለድ ጋር ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ተወስኗል።

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን እንዲችል ብለናል።

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ። የመቐለ ከተማ ሠሜን ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል። ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ታ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን

ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ያየዉ የወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 13075 ላይ አከራክሮና ምስክሮቻቸዉን ሰምቶ በቀን 22/09/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40/7 መሰረት መሬት የሕዝብና የመንግስት ሀብት በመሆኑ ለመሸጥ ለመለወጥ ስለማይቻል በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ የሽያጭ ውል ሕገ መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስና አመልካች የሰራዉን ቤት አፍርሶ እንዲወስድ በማለት ወስኗል።አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 12167 ላይ በቀን 07/10/2011 ዓ/ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥ 337 መሰረት በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዟል።

በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ በመ/ቁጥር 117434 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 21/01/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርብ ማይ ተህሊት ቀበሌ አዲስ የተመሰረተች ከተማ እንደሆነች በመግለጽ አመልካች በዚህ ከተማ የሚገኝ የመኖሪያ ቤትና ቦታ ይልቀቅልኝ በማለት ዳኝነት ቢጠይቅም በስር ፍርድ ቤት አዲስ የተመሰረተች ከተማ ናት ወይስ አይደለችም የሚለው አልተጣራም። በተጨማሪ ተጠሪ በክሱ ውስጥ አዲስ የተመሰረተች ከተማ መሆኗን ቢገልፅም እንኳን በተግባር ግን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ ባሉት ከተሞች ማይ ተኸሊት አዲስ የተመሰረተች ከተማ ሆና በአዲስ ከተማነት የተካተተች አለመሆኗ ተረጋግጧል በማለት የሽያጭ ውሉ የገጠር መኖሪያ ቦታ ሽያጭ የሚመለከት በመሆኑ ውሉ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ አመልካች የሰራዉ ቤት ካለ አፍርሶ ይውሰድ በሚል በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነዉ በሚል በማጽናት ነገር ግን አመልካች ቦታውን የገዛበትን ብር 7700.00 ተጠሪ እንዲመልስ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል። አመልካች በቀን 30/01/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ አግባብ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ።

አመልካች የገዛሁት የገጠር መሬት ሳይሆን ለተጠሪ በከተማ ለድርጅት ተብሎ በተሰጠው ቦታ ላይ የተሰራ ቤት ከነ ይዞታው ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የገጠር መሬት አይሸጥም ብለው ከሚያከራክረን ጭብጥ ዉጭ ውሳኔ ሰጥተዋል ። በግራ ቀኝ በቀረቡ ምስክሮች የተረጋገጠዉም በከተማ የተሰራ ቤት የተሻሻጥን መሆኑን ነው።ቤትና ቦታው መልቀቅ አለብህ የሚባል ከሆነ ተጠሪ ፈቅዶ እና ሳይቃወመኝ 2 ትላልቅ ቤቶች ብር 360,000.00 የሚገመት ስለሰራሁበት በፍ/ሕግ ቁጥር 1179/2 መሰረት የዚህን ግምት እና የቤቱን የግዢ ዋጋ ብር 7,700.00 ተጠሪ ከወሰደበት ከቀን 12/05/19999 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ አለመወሰኑም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም በመጠየቅ አቤቱታዉን አቅርቧል።

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በዚህ ጉዳይ የሽያጭ ውሉ የተደረገው በከተማ ይሁን በገጠር ባልተለየበት እና አመልካች ቤትና ይዞታ ገዛሁ በማለት እየተከራከረ ውሉ ፈርሶ የገነባዉን ቤት አፍርሶ ይልቀቅ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731 እና 1179 አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 02/06/2012 ዓ/ም የተጻፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል።

አመልካች በቦታው ላይ 360,000.00 ወጭ አድርጌበታለው ይበል እንጂ የተሰራው ቤት በሁለት ገፅ የድንጋይ ካብ ሲሆን በሁለት ገፅ ደግሞ ግድግዳ እና በ25 ቆርቆሮ ሁለት ቢያጆ ድንጋይ እና ግድግዳው የገጠር እንጨት ነው። ይህም በትክክል ቢገመት የወጣዉ ወጪ ከብር 6000-7000 ቢሆን ነው። ቦታው የገጠር መሬት ስለሆነ አይሸጥም አይለወጥም። ውላችን በ2000 ዓ/ም ፈርሶ ቤቱን የሰጠኝን ገንዘብ እራሰ በቦታዉ የሰራሁትን ቤት እያከራየ እንዲወስድ ተስማምተን ገንዘቡን መዉሰዱን በወረዳ ፍርድ ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል። ቤቱንም ከሁለት አመት በፊት ለቆ አስረክቦኛል። ግምት እንኳ መክፈል ካለብኝ የገጠር ቦታ ስለሆነ በሽማግሌዎች የተገመተውን ብር ውሰድ ብዬው ፈቃደኛ አይደለም። ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል።አመልካችም በቀን 21/06/2012 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታ በማጠናከር ተከራክሯል።

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሎ ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን ከግራ ቀኝ ክርክር፣ ከስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ይዘት እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመርነውም ግራ ቀኙን ያከራከረዉንና የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚፈልገዉ ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ከአመልካች ጋር አዲስ በተመሰረተችዉ ማይ ተኽሊት ከተማ ዉስጥ ለመኖሪያ ተብሎ በ1994 ዓ/ም በተሰጠዉ ቦታ ላይ የሰራዉን አንድ ክፍል መኖሪያ ቤትና ቦታ ለአመልካች በ1999 ዓ/ም ስለሸጥኩ መሬት መሸጥና መለወጥ ስለማይቻል ዉሉ ከመነሻዉ ፍርስ(void) ስለሆነ አመልካች በይዞታው ላይ የሰራውን ቤት አፍርሶ መሬቱን እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በሚል የጠየቀዉን ዳኝነት በተመለከተ የተሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ። አመልካች ከስር ጀምሮ የቤት ሽያጭ ዉሉ ባዶ መሬት ለመግዛት የተደረገ እንዳልሆነ እና በቦታዉ ላይ ከፍተኛ ገንዘብ አዉጥቼ ተጠሪ ሳይቃወመኝ ተጨማሪ 2 ክፍል ቤቶች ስለሰራሁ ዉሉ ሊፈርስ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል።የክልሉ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የወሰኑት ዉል የተደረገዉ በሕገ መንግስቱ የተከለከለዉን መሬት እንዳይሸጥ የተደነገገዉን ክልከላ በመተላለፍ የተደረገ በመሆኑ የዉሉ ጉዳይ ሕገወጥ ነዉ በማለት እንደሆነ ተገንዝበናል።

እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት እና በተመሳሳይ በትግራይ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/3 ስር የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ በመሆኑ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል። በዚህ መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ ባዶ መሬት በመሸጥ የሚፈጸም ዉል ሕገ መንግስታዊ የሆነዉን መሬት አይሸጥም የሚለዉን ክልከላ የሚጥስ በመሆኑ የጸና ዉል እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታ ተደርጎ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1678/ለ ስር የተደነገገዉን የዉሉን ጉዳይ ሕጋዊ የመሆን ሁኔታ የማያሟላ ስለሚሆን በፍ/ብ/ሕግ/ቁጥር 1716 እና 1808/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ዉሉ የተደረገበት ጉዳይ ከሕግ ዉጭ ስለሆነ ከመነሻዉ ዋጋ አልባ ዉል እንደሆነ የሚቆጠር ወይም ደግሞ

17/10/12

ጥበቃ ያለዉ መብት ያለዉ በመሆኑ በመሬት ላይ የተገነባዉን ቤት ለመሸጥ የሚደረግ ዉል ጉዳይ ሕገወጥ ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም። ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለግራ ቀኝ ክርክር መነሻ የሆነዉን የቤት ሽያጭ ዉሉን ጉዳይ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ሕገ ወጥ ነዉ በማለት መወሰናቸዉም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና የቤት ሽያጭ ዉል ነዉ በማለት ዉሉ ሕገ ወጥ ስለሆነ ዋጋ አልባ ነዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመዉን ስህተት ማረም ሲገባዉ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ የተሸጠዉ ቤት አዲስ በተመሰረተ ከተማ ዉስጥ እንደሚገኝ በተጠሪ ክስ ላይ ተግለጾ እያለና ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ባልቀረበበት በገጠር የእርሻ መሬት ላይ ቤት ተሰርቶ ከሕግ ዉጭ በሆነ አኳኋን የሽያጭ ዉል እንደተፈጸመ በመቁጠር የቤት ሽያጭ ዉሉ ጉዳይ ከሕግ ዉጭ ነዉ በማለት እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራርና የሕግ አተገባበር ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል።

## ዉ ሳ ኔ

1. የፀለምቲ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13079 ላይ በቀን 22/09/2011 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የሰሜን ምእራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12167 ላይ በቀን 07/10/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር በመ/ቁ 117434 ላይ በቀን 21/01/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥ 348/1 መሰረት ተሽረዋል።

2. በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል የጸና ነዉ በማለት ወስነናል።

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል።

## ት እ ዛ ዝ

1. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ።
2. መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቁ